ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ                                    መሐረም 28/1440 ሂ.
አውቃፍ ሚኒስትር                                    ሴፐተምበር 27/2019 ግ.

# የአሉባልታና ግንዛቤን የማዛባት አደጋ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَقُولُوا قَوْلًا سَدِيدًا * يُصْلِحْ لَكُمْ أَعْمَالَكُمْ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ وَمَنْ يُطِعِ اللَّهَ وَرَسُولَهُ فَقَدْ فَازَ فَوْزًا عَظِيمًا}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ፡፡ ሥራዎቻችሁን ለእናንተ ያበጅላችኋልና፡፡ ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምርላችኋል፡፡ አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዝም ሰው በእርግጥ ታላቅን እድል አገኘ፡፡) ማለት ነው
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

ከእውነትና ከከንቱ መካከል ያለው ትግል ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር እንደጀመረ ይታወቃል፡፡ አንድሁም አላህ (ሱ.ወ.) ምድርንና በውስጧም ያለውን ነገር ሁሉ እስከሚወርስበት እስከት ትንሳኤ እለትም ይቀጥላል፡፡ የከንቱ ትግባር ባለቤቶች ከእውነት ተግባር ባለቤቶች ጋር በሚያደርጉት ትግል የሚጠቀሙበት አበይ መሳሪያ አሉባልታን መፍጠርና ማስፋፋት መሆኑን ሊ ቃውንት ይጠቁማሉ፡፡
የሚነበብ፣ የሚሰማም ይሁን የሚታይ ቃል መከበር ያለበት አደራና ታላቅ ሃላፊነት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አሉባልታ ልበ በሽተኛ ሰው ወይም በምስጢር የሚሰራ የተንኮል ሃይል ከሰዎች መካከል የሚያናፍሱት ቃል እንጂ ሌላ ነገር አይደልም፡፡ ከዚያም በኋላ ያለማረጋገጥና ያለማስረጃ ልሳናት ከቦታ ወደቦታ ሲያሸጋግሩት በአእምሮዎችና በልቦናዎች መካከል አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በዚህ መልኩም አፍራሽ እሳቦቶችና ብልሹ እምነቶች ይስፋፉና ህብረተሰቡ በጭንቀትና በጥርጣሬ ውሎ ያድራል፡፡ ብሎም ጸጥታ ይደፈርሳል፣ ከሰዎች መካከል ያለው አመኔታም ይዳከማል፡፡ በመሆኑም የአንድ ህዝብ አካል አንዱ ሌላውን ይጠራጠራል በክህደትም ይወነጃጀላሉ፡፡ ስለዚህም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው ለመዋሸት የሚሰማውን ሁሉ ማውራቱ በቂው ነው፡፡) አንድ ሰው የሰማውን ሁሉ ማውራቱ የውሸት ዓይነት ይሆናል በሱም በመጭው

አለም ይቀጣበታል ከተባለ ያልሰማውንና ያለየውን የሚያወራ ሰው ቅጣት እንዴት ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅትም፡፡

የአስልምና እምነት ስለአሉባልታና አሉባልታን ስለሚያስፋፉ ሰዎች ጥብቅ አቋም ወስዷል፡፡ አሉባልታ የእምነቱ መሰረቶች የሆኑት የመልካም ስነ ምግባርና የጠቃሚ እሴቶች ተፃራሪ ጠባይ መሆኑን እምነቱ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ለዚህም የእምነቱ ተከታዮች በማህበረሰቡ መካከል ህውከትንና ብጥብጥን ከሚያስፋፋ ወሬ ምላሳቸውን እንዲጠብቁ እንድሁም ቃላቸውን እውነተኛ እንዲያደርጉ ህውከትን በማስፋፋት ተሳታፊ እንዳይሆኑ ወደጆሯቸው የሚደርሱ ቃላትን ትክክለኛነት እንዲያጣሩ አዟል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَكُونُوا مَعَ الصَّادِقِينَ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ከእውነተኞቹም ጋር ኹኑ፡ ) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{ مَا يَلْفِظُ مِنْ قَوْلٍ إِلَّا لَدَيْهِ رَقِيبٌ عَتِيدٌ}

ትርጉሙም (ከቃል ምንም አይናገርም በአጠገቡ ተጠባባቂና ዝግጁ የኾኑ (መላእክት) ያሉበት ቢኾን እንጅ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَقْفُ مَا لَيْسَ لَكَ بِهِ عِلْمٌ إِنَّ السَّمْعَ وَالْبَصَرَ وَالْفُؤَادَ كُلُّ أُولَئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْئُولًا}

ትርጉሙም (ለአንተም በርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር አትከተል፡፡ መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙዓዝ ኢብን ጀበል ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የእስልምናን ግዴታዎችና የመልካም ነገር በሮችን ከዘረዘሩላቸው በኋላ እንድህ ያሏቸው መሆኑን አውርተዋል፡ (ብትፈልግ የነገሩን ራስና ዋልታ እንድሁም የሻኛውን ቁንጮ ልነግርህ እችላለሁ፡፡) ሙዓዝም አዎን የአላህ መልክተኛ ሆይ አሉ፡ እሳቸውም እንድህ አሉ፡ (የነገሩ ራስ እስልምና ነው፡፡ ዋልታው ደግሞ ስግደት ነው፡፡ የሻኛው ቁንጮ ደግሞ በአላህ መንገድ መታገል ነው፡፡ ብትፈልግም ይህን ሁሉ በእጅህ የምታስገባበትን ነገር አነግርሃለሁ፡፡) ሙዓዝም እሱ ምንድን ነው ያላህ መልክተኛ ሆይ! አሉ፡፡ ከዚያም ነብያችን ጣታቸውን ወደምላሳቸው አስገቡና ይህን ተቆጣጠር አሉ፡፡ ሙዓዝም ያለህ መልክተኛ ሆይ! እኛ በምላሳችን ስለምንናገረው ነገር ተጠያቂዎች እንሆናለን እንዴ? አሉ፡፡ እሳቸውም (እናትህ ትጣህና ሰዎችን በሀገነም በአፍንጫቸው የሚደፋቸው በምላሳቸው የሚጭዱት እንጂ ሌላ ነገር ነው እንዴ? ) አሉ፡፡

አሉባልታን ማናፈስና ማስፋፋት ጸጥታን በማደፍረስ፣ የሀገረን አንድነት አደጋ ላይ በመጣል፣ የኢኮኖሚ ልማቱን በማዳከምና መረጋጋቱን ኢላማ በማድረግ እንድሁም በህዝቡ ዘንድ በተለይም ደግሞ በወጣቱ መንፈስ የተስፋ መቁረጥና የመጥፎ ገድ መንፈስን በማሰራጨት መናፍቃን ወደጉዳያቸውና አላማቸው ለመድረስ የሚከተሉት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَئِنْ لَمْ يَنْتَهِ الْمُنَافِقُونَ وَالَّذِينَ فِي قُلُوبِهِمْ مَرَضٌ وَالْمُرْجِفُونَ فِي الْمَدِينَةِ لَنُغْرِيَنَّكَ بِهِمْ ثُمَّ لَا يُجَاوِرُونَكَ فِيهَا إِلَّا قَلِيلًا}.

ትርጉሙም (መናፍቃንና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ (የአመንዝራነት) በሽታ ያለባቸው በመዲናም ውስጥ (በወሬ) አሸባሪዎቹ (ከዚህ ሥራቸው) ባይከለከሉ በእነርሱ ላይ በእርግጥ እንቀሰቅስሃለን፡፡ ከዚያም በእርሷ ውስጥ ጥቂትን እንጂ አይጎራበቱህም፡፡) ማለት ነው፡፡

አሉባልታ በነብያችንም (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ ሳይቀር ጉዳት ያደረሰ ከጦርነት ዘዴዎች አንደኛው ነው፡፡ የመካ አጋሪዎች ሰበካቸውን ኢላማ በማድረግና ገጽታቸውን በማበላሸትና ስማቸውን በማጥፋት አሉባልታዎችን እያናፈሱ ነብያችንን ይዋጉ ነበር፡፡ ከሰዎችም መካከል በሀሰት ነብያችን ድግምተኛ መሆናቸውን አናፈሱ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَقَالَ ٱلْكَافِرُونَ هَذَا سَاحِرٌ كَذَّابٌ}

ትርጉሙም (ከሓዲዎቹም «ይህ ድግምተኛ (ጠንቋይ) ውሸታም ነው» አሉ፡፡ ) ማለት ነው፡፡ በቅጥፈትም ገጣሚና አብድ መሆናቸውን አናፈሱ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَيَقُولُونَ أَئِنَّا لَتَارِكُو آلِهَتِنَا لِشَاعِرٍ مَجْنُونٍ}

ትርጉሙም (እኛ ለዕብድ ባለቅኔ ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው ነን? ይሉም ነበር፡፡) ማለት ነው፡፡ በሌላም ጊዜ ካህን ነው ሲሉ አናፈሱ፡፡ ያን ጊዜ አላህ እንድህ በማለት መልሶላቸዋል፡

{إِنَّهُ لَقَوْلُ رَسُولٍ كَرِيمٍ * وَمَا هُوَ بِقَوْلِ شَاعِرٍ قَلِيلًا مَا تُؤْمِنُونَ * وَلَا بِقَوْلِ كَاهِنٍ قَلِيلًا مَا تَذَكَّرُونَ *تَنزِيلٌ مِنْ رَبِّ الْعَالَمِينَ}.

ትርጉሙም (እርሱ (ቁርኣን) የተከበረ መልክተኛ ቃል ነው፡፡ እርሱም የባለቅኔ ቃል (ግጥም) አይደለም፡፡ ጥቂትን ብቻ ታምናላችሁ፡፡ የጠንቋይም ቃል አይደለም፡፡ ጥቂትን ብቻ ታስታውሳላችሁ፡፡ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

በእሑድ ጦርነት ቀንም አጋሪዎች ነብያችን ሞተዋል የሚል አሉባልታ አናፈሰው ነበር፡፡ ይህውም ሰዎች ጥለዋቸው እንዲሸሹና ኃይላቸውም እንዲዳከም በማሰብ ነበር፡፡ በእርግጥም ከሙስሊሞች መካከል ህውከት ተፈጠረ፡፡ የመንፈሳዊ ኃይላቸውም ተዳከመ፡፡ ከፊሎቻቸውም ሸሹ፡፡ ከፊሎችም መሳሪያ ጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከፊሎቹ ከነብያችን ጋር በሙሉ እምነት ያለመንቀሳቀስ ተረጋግተው ቆይተዋል፡፡

በሐምራእ ኢል አሰድ ጦርነትም ከሃዲዎች የቁረይሽ ጎሳዎች ነብያችን ለመዋጋት፣ መዲናን ለመውረርና አስልምናን ከስር መሰረት ለማጥፋት ከፍተኛ ጦር አዘጋጅተዋል የሚል አሉባልታ አናፍሰው ነበር፡፡ ሙስሊሞች ግን በዚህ አሉባልታ ያለመበገር በሃይማኖታቸው ጸንተው ነበር፡፡ በመሁኑም አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል አመስግኗቸዋል፡

{الَّذِينَ قَالَ لَهُمُ النَّاسُ إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ إِيمَانًا وَقَالُوا حَسْبُنَا اللَّهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ * فَانْقَلَبُوا بِنِعْمَةٍ مِنَ اللَّهِ وَفَضْلٍ لَمْ يَمْسَسْهُمْ سُوءٌ وَاتَّبَعُوا رِضْوَانَ اللَّهِ وَاللَّهُ ذُو فَضْلٍ عَظِيمٍ}.

ትርጉሙም (እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፡- «ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው» ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው «በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ!» ያሉ ናቸው፡፡ ከአላህም በኾነ ጸጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ኾነው ተመለሱ፡፡ የአላህንም ውዴታ ተከተሉ፤ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡

የእስልምና ጠላቶች የስግዴት ቂብላ ከበይተል መቅድስ ወደ በይቱላሂልሐራም በተዛወረበት ጊዜ አሉባልታ መናፈስ ጀመሩ፡፡ አይሁዶች ወደበይቱልሐራም ስለመዞር እውነተነት የመጠራጠሩን ተግባር በቅንጂት ያከናውኑ ነበር፡፡ እናንተ ሙስሊሞች የመጀመሪያው ቂብላችሁ እውነተኛ እንደሆነ የምታምኑ ከሆናችሁ እነሆ እውነትን ትታችኋል፡፡ የመጀመሪያው ቂብላችሁም ከንቱ በመሆኑ የምታምኑ ከሆናችሁ ደግሞ ከዚህ በፊት የሰራችሁት ኢባዳችሁ ከንቱ ነው፡፡ መሀሐመድም በእውነት ነብይ ቢሆን ኖሮ የቀደምት ነብያትን ቂብላ ትቶ ወደሌላ ባልዞረና ዛሬ የፈጸመውን ነገር ነገ በተጻራሪው መልኩ ባላከናወነው ነበር እያሉ የህዝቡን አመለካከት አዘበራረቁ፡፡

መናፍቃን በበኩላቸው እነዚህ ሙስሊሞች ምነካቸው ወደአንድ ቂብላ ሲሰግዱ የነበር አሁን ደግሞ ተውት እያሉ መሳለቅ ጀመሩ፡፡ አጋሪዎችም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ በሃይማኖቱ ግራ ተጋብቷል ወደቂብላችን እንደተመለሰ ሁሉ ወደሃይማኖታችንም ሳይመለስ አይቀርም የሚል ወሬ አናፈሱ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ቀድሞ እነዚህ ሞኞች የሚሉትን ሁሉ ለመልከተኛው በማሳወቁ ይህን አሉባልታ በማስተባበል የምእምናን መንፈስ አረጋግቶ እምነታቸውንም አጠንክሯል፡፡ እንድሁም በሑነይን ጦርነት ቀን ነብያችን እንደተገደሉ አሉባልታ ተናፍሶ ነብያችን ይህን አሉባልታ በራሳቸው ቁመው (ሀሰት አይደለም እኔ ነብይ ነኝ እኔ የአብደልሙጠሊብ ልጅ ነኝ፡፡) በማለት ተጋፍጠዋል፡፡

አሉባልታን በመመላስና በማስፋፋት ነፍስና ንብረት እንደሚጠፋ ክብር እንደሚነካና ሕይወት እንደሚበጣበጥ ለማንም ልበኛ ድብቅ ነገር አይሆንም፡፡ ለዚህ ጉዳይ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) በከሊፋው ኡስማን ኢብን አፋን መገደል ጉልህ መረጃ አለን፡፡ አይሁዳዊው አብደላ ኢብን ሰበእ ባናፈሰው አሉባልታ ምክኒያት አረመኔዎች ከበቧቸው፡፡ በራሳቸው ገንዘብ ከገዙት ሙእታ ውሃ ጉድጓድ እንዳይጠጡም ከለከሏቸው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) የኡስማን ባለቤት ናኢላህ የሚከተለውን አውርተዋል፡፡ ኡስማን ከተገደሉበት ቀን በፊት ቀኑን ጹመው ዋሉ፡፡ በማፍጠሪያ ሳዓት ውሃ ቢጠይቁ ጊዜ ከለከሏቸው፡፡ ሳያፈጥሩም ተኙ፡፡ የጾም መያዣ ሳዓት ሲደርስ ወደጎረቤት ሴቶች ሄጀ ውሃ ለመንኩኝ፡፡ አነሱም አንድ ኮዳ ውሃ ሰጡኝ፡፡ መጣሁና ነቅነቅ ሳደርጋቸው ነቁ፡፡ ይህውና የመጠጥ ውሃ አመጣሁ አልኳቸው፡፡ ቀጥ አሉና ወደኀህ ተመለከቱ፡፡ እኔ ጾም ይዤ አድሪያለሁ አሉ፡፡ ቀጥለውም ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ውሃ ይዘው በዚህ ጣራ በኩል ብቅ ብለው (ኡስማን ሆይ! ጠጣ) አሉኝ፡፡ እስከምረካም ጠጣሁኝ (ጨምር) አሉኝ፡፡ ሆዴ እስከሚሞላ ጠጣሁ፡፡ ከዚያም እንድህ አሉኝ፡ (እነዚህ ሰዎችኮ ይበዙብሃል፡፡ ሆኖም ብተዋጋቸው ድልን ትቀዳጃለህ፡፡ ብትተዋቸው ግን ከኛ ጋር ታፈጥራለህ፡፡) በዚያን ቀን ገቡና ገደሏቸው፡፡

ባለነብት ዘመን ደግሞ የመገናኛ ዘዴዎችና ቴክኖሎጂ በፍጥነት እየተለወጠ በመምጣቱ ምክኒያት በርካታ ሁኔታዎች ተቀይረዋል፡፡ የዚህ እርኩስ ሥራ ቅርጾችና ገጽታዎች የተለያዩና በርካታዎች ሆነዋል፡፡ በዚህ ዘመን የአሉባልታ ስርጭት እጅግ ፈጣን ተጽእኖውም ሰፊ ሆኗል፡፡ ይልቁንም ከጦርነት መሳሪያዎችና ዘዴዎች አንዱ በመሆኑ ጦርነት እንደተለመደው በመሳሪያ፣ በደህንነት ክትትልና በመረጃ ማሰባሰብ ብቻ የተወሰነ አልሆነም፡፡ ጦርነት በአሁኑ ወቅት አሉባልታንና ግንዛቤ ማወዛገብን በአደገኛ መሳሪያነት ይጠቀምበታል፡፡ አሱም በተለያዩ ተቋማት አማካይነት ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥበት ታዋቂ መሳሪያ ሆኗል፡፡ ለሱም የሰለጠነ የኤሌክተሮኒክስ ግብረ ኃይልም እየተመደበለት ከፍተኛ የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚና የመንፈሳዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ህዝብ በመንግስት ላይ አመጽ እንዲያስነሳ፣ የህዝብ አርኣያ አካላትም ስም እንዲጠፋ፣ የተመዘገቡ ስኬቶችን በማቃለል ዘርፍ የሚደረጉ ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶች የሰዎችን ወቅታዊ ፍላጎት መሰረት ከአደረገው የአሸባሪ ቡድኖች የተቀናጀ የመበታተን መካኒዝም ጋር ተደምሮ የህዝቡን ጽኑ ፍላጎት በመሰበር፣ የባለስልጣናትን ሞገስ በመግፈፍ፣ በሀገር ወዳድ ሊቃውንትና ተመራማሪዎች አመኔታ ጉዳት በማድረስ፣ እውነተኛ መርሀቸውን አንለቅም ለአሉ ታማኝ አገር ወዳድ ወገኖች ዛቻ በማስተላለፍ ወደከህደት ወገን እንዲቀላቀሉ በማድረግና እጅ ሰጥተው እንዲምበረከኩ ከዚያም ሁሉም እነሱን ተከትሎ እንዲምበረከክ ይህ ነው የማይባል ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ይህን ሁሉ አደገኛ ሞገድ ለመቋቋም ጠንካራ ሀገራዊ ፍቅርና ወሰን የለሽ የፈጣሪ እምነት የሚጠይቅ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ጥቂት የሚባሉ በእውነተኛ መረጃ ያልተደገፉ ወሬዎችን፣ እስታቲስቲኮችንና ትረካዎችን ማስተላፋቸውን እንደቀላልነገር ይመለከቱታል፡፡ በዚህም አሉባልታና ህውከት በማሰራጨት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ አንድ ሰው መሰረት ቢስ ቃልን በመናገር፣ በመፃፍ ወይም በማስተላለፍ በትንሳኤ ቀን ከፍተኛ ቅጣት ሊደርስበት ይችላል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ባሪያ እንድሁ ልብ ሳይል አላህን የሚያስደስት ቃል ይናገርና በሱ ምክኒያት አላህ ወደከፍተኛ ደረጃዎች ያደርሰዋል፡ ፡ አንድ ባሪያ ደግሞ እንድሁ ልብ ሳይል አላህን የሚያስቆጣ ቃል ይናገርና በሱ ምክኒያት በገሀነም ይዘፈቅበታል፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

*        *        *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የእስልምና እምነት ማህበረሰቡን ከአሉባልታ አደጋ ለመጠበቅ በሚከተሉት ነጥቦች አማካይነት ጥበብ የተሞላበት ስርአት አስቀምጧል፡

* አንድ ወሬ ስንሰማ በማህበረሰቡ መካከል ከማሰራጨታችን በፊት ማጣራት አለብን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَى مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}

ትርጉሙም (እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጸኞች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡”) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ዝግታ ከአላህ (ዐ.ወ.) ነው፡፡ መቻኮል ደግሞ ከሰይጣን ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (በማንኛውም ነገር ዝግታ ደግ ነው በመጭው ዓለም ሥራዎች ሲቀር፡፡)

* በሚነበብ፣ በሚሰማና በሚታይ የመገናኛ ዘዴ አማካይነት አሉባልታዎችን አለመደጋገም፡፡ አሉባልታ የሚደጋግም ልሳን፣ የሚያዳምጥ ጆሮና የሚቀበል መንፈስ ሲያገኝ በፍጥነት ይስፋፋል፡፡ አላህ (ሶ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِذْ تَلَقَّوْنَهُ بِأَلْسِنَتِكُمْ وَتَقُولُونَ بِأَفْوَاهِكُمْ مَا لَيْسَ لَكُمْ بِهِ عِلْمٌ وَتَحْسَبُونَهُ هَيِّنًا وَهُوَ عِنْدَ اللَّهِ عَظِيمٌ }

ትርጉሙም (በምላሶቻችሁ በምትቀበባሉት ጊዜ ለእናንተም በእርሱ ዕውቀት በሌላችሁ ነገር በአፎቻችሁ በተናገራችሁና እርሱ አላህ ዘንድ ከባድ ኀጢአት ኾኖ ሳለ ቀላል አድርጋችሁ ባሰባችሁት ጊዜ (ከባድ ቅጣት በነካችሁ ነበር)፡፡ ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ ( በአላህና በመጨረሻውም ቀን የሚያምን ሰው በጎረቤቱ ላይ ጉዳት አያድረስ፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው እንግዳውን ያክብር፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው ደግን ነገር ይናገር ወይም ጸጥ ይበል፡፡)

* ለሌሎች መልካም ግምትን መስጠትና በነሱ ላይ ወንጀል ለመሰንዘር አለመቸኮል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ لَوْلَا إِذْ سَمِعْتُمُوهُ ظَنَّ الْمُؤْمِنُونَ وَالْمُؤْمِنَاتُ بِأَنْفُسِهِمْ خَيْرًا وَقَالُوا هَذَا إِفْكٌ مُبِينٌ}

ትርጉሙም ((ውሸቱን) በሰማችሁት ጊዜ ምእምናንና ምእምናት በጎሶቻቸው ለምን ደግን ነገር አልጠረጠሩም ለምንስ ይህ ግልጽ ውሸት ነው አላሉም፡፡)

ማንኛውም ሙስሊም ሌሎችን በበጎ መገመትና ለተግባራቸውም መልካም ግምት እንዲሰጥ ታዟል፡፡ ሰዎችን በመጥፎ መገመት ሕይወትን የሚያወዛግብ አውዳሚ በሽታ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ከዚህ አደገኛ በሽታ አስጠንቅቀዋል፡ (አደራ በመጥፎ ከመገመት ተጠንቀቁ፡፡ በመጥፎ መገመት የሀሰት ወሬ ነው፡፡ የሰዎችን ወሬ አታዳምጡ ነውራቸውንም አትከታተሉ አትመቀኛኙ ጀርባም አትስጣጡ አትጠላሉም ወንድም ተማማች የአላህ ባሪያዎች ሁኑ፡፡)

* ለነገሮች ብያኔ ለመስጠት ያለመቻኮል ነገሮችን ለማጣራትና ለማረጋገጥ በባለልምዶችና በባለሞያዎች መታገዝ፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.ወ.) የመናፍቃንን ሁኔታ እንድህ በማለት ገልጹዋል፡

{وَإِذَا جَاءَهُمْ أَمْرٌ مِنَ الْأَمْنِ أَوِ الْخَوْفِ أَذَاعُوا بِهِ وَلَوْ رَدُّوهُ إِلَى الرَّسُولِ وَإِلَى أُولِي الْأَمْرِ مِنْهُمْ لَعَلِمَهُ الَّذِينَ يَسْتَنْبِطُونَهُ مِنْهُمْ وَلَوْلَا فَضْلُ اللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُ لَاتَّبَعْتُمُ الشَّيْطَانَ إِلَّا قَلِيلًا }

ትርጉሙም (ከጸጥታ ወይም ከፍርሃት አንዳች (ወሬ) በመጣላቸውም ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ፡፡ ወደ መልክተኛውና ከእነርሱ ወደ ትዕዛዙ ባለቤቶች (ወደ ዐዋቂዎቹ) በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ (ነገሩን) የሚያውጣጡት ባወቁት ነበር፡፡ በእናንተም ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ ከጥቂቶች በስተቀር ሰይጣንን በተከተላችሁ ነበር፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ማለትም እንነሱ በመዲና ማህበረሰብ ችግር ለማድረስ አድፍጠው ነበርና በሙስሊሞች ደህንነት ጉዳት የሚያደርስ እንድሁም ፍራት የሚያስከትል ወሬ ሲሰሙ በማህበረሰቡ ዘንድ ፍርሃት፣ ጭንቀትና ብጥብጥ እንዲሰፍን በፍጥነት ያናፍሱት ነበር፡፡

ለሃይማኖቱ ቅናት ያለበትና ለሀገሩ ታማኝ የሆነ ምእምን ሁሉ የዚህ ኣይነቱን አደገኛ አሉባልታ በማስተባበል ለመቋቋም አፈሩን አራግፎ ይነሳ፡፡ ነብያችን (ሱ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በወንድሙ ክብር ላይ የተሰነዘረን ስም ማጥፋት የመለሰ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን እሳትን ከፊቱ ይመልስለታል፡፡) በመጨረሻም ቃል በትንሳኤ ቀን አላህ (ዐ.ወ.) ፊት የምንጠይቅበት አደራ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ሁላችንም ጠላቶቻችን ጀኔሬሽን አራትና አምስትን፣ አሉባልታን፣ ማንኛውንም ሀገራዊ ነገርን ቅርጽ ማጥፋትን መሰረት በማድረግ ሀገሮቻችንን ስኬት አልባ ለማድረግ ወይም ለመጣል አለዚያም ለመበታተን እየተዋጉን መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡ ውጊያውም እጅጉን የተፋፋመ በመሆኑ በጠላቶቻችን ደባ እንዳንጠለፍ በራሳችን አንድሁም በመሪዎቻችን ሙሉ እምነት ሊኖረን ይገባል፡፡ ስለዚህ ለጠላቶቻችን ጆሯችንን መስጠት የለብንም፡፡ እነሱ ደህንነታችንነ አደጋ ላይ ለመጣል፣ ሞራላችንንም ዝቅ ለማድረግ፣ የተስፋ መቁረጥ መንፈስም እንድስፋፋ ጥረት አያቆሙምና ለመላ ማህበረሰቡ በተለይም ደግሞ በወጣቶቻችን ዘንድ ብቁ ግንዛቤ እንድኖርና የተደቀኑ ችግሮችን መጠን እንዲያውቁ በችግሮች መፍትሄም ተሳታፊ እንድሆኑ መታገል አለብን፡፡

ጌታችን ሆይ! ጠባያችንን አሳምርልን ሀገራችንንም ጠብቅልን የምትወደውንም ነገር እንድንሰራ ሰኬትን ስጠን፡፡

***